## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian Peoples Revolutionary Party (EPRP)

# አገር አድን ዘመቻ ግብረ ኃይል

አንድነቷና ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያን ጀግኖች አባቶቻችን ለቀጣዩ ትውልድ ያስረከቡት እኔ ለሀገሬ አያገባኝም በማለት ሳይሆን በአንድነትና በመተባበር ባደረጉት ትግልና በከፈሉት ክቡር መስዋእትነት ነበር። ይህ ትውልድም ሀገራችን ከወደቀችበት ሁኔታና ከደረሰባት አደጋ ለማዳን በአንድነት የመነሳትና የመረባረብ ኃላፊነት አለበት ።

ይህ ትውልድ የታሪክ ባለአደራ መሆኑን በመገንዘብና ሀገራችን ሊበታትኗት ከተነሱት ከሃዲዎችና ከጎጠኛ ኃይሎች ሴራ ለማዳን ቆርጦ መነሳት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የሰሜን አሜሪካ ኢሕአፓ ክፍል እነሆ **አገር አድን ዘመቻ ግብረ ኃይል** በማቋቋም የሀገራችንን ሉአላዊነት እንዳይደፈር መድብለ ፓርቲ እውን እንዲሆን፣ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም፣ ዜጎች የመናገር ሰላማዊ ሰልፍ፣ የመጽሃፍና የሀገራቸው የፖለቲካ ወሳኝ እንዲሆኑ፣ ኢትዮጵያዊያን በሰደት እንዳይሰቃዩና ከሃገራቸው እንዳይፈናቀሉ፣ ሕዝቡን ለጦርነት ማገዶ እንዳይዳረጉ፣ በሃይማኖት እንዳይከፋፈሉ፣ ገበሬው ለሚአርሰው መሬት ባለቤት እንዲሆን እየታገለ ይገኛል። ትግሉን ለማጠናከርና ውጤት እንዲያገኝ ለማድረግ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከመቼውም በበለጠ እጃችሁን የምትዘረጉበት ጊዜ አሁን ነው ይላል። ይህንንም በተግባር ለመተርጎም አገር አድን ዘመቻ ግብረ ኃይል አቋቁሟል።

ለዚህ የትግል ጥሪ መሳካት እያንዳንዱ ሀገር ወዳድ መሰለፍና መቆም አለበት። በሀገራችን የተጀመረውን ለውጥ የታለመለትን ግብ እንዲመታ የሁላችን ትብብርና እርዳታ ይጠይቃል። በተለይ ለሚታገል ድርጅት ገንዘብ ወሳኝ መሳሪያ ነው። ያለገንዘብ የሚገባደድ ትልምና እቅድ የለም። የሰሜን አሜሪካ ኢሕአፓ ክፍል ለዚህ ወሳኝ ዓላማ ብዙ ጥረቶችን አቅዶ **በሀገር አድን ዘምቻ ግብረ ኃይል** የገንዘብ ድጋፍና እርዳታ እያሰባሰበ ይገኛል። የሀገራችን ችግር መፍትሄ ፈላጊዎች እኛው ኢትዮጵያውያን መሆናችን ግልጽ ስለሆነ ጥሪውን መቀበልና የተቻለንን ማድረግ አገራዊ ግዴታችንን በመውጣት መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰብዐአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተገፎ፣ በመላ ሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምና የኑሮ ዋስትና ጠፍቶ፣ የሥራ እድልና የማህበራዊ ኑሮው እያቆለቆለ በሄደበት፣ ከድንቁርና፣ ከድህነት ያልተላቀቀው ወገናችን ስቃይ እየባሰ በሚታይበት፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች ለጎጠኞች ብቻ በሆነበት፣ ፍትህና እኩልነት በጠፋበት ማንኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ ይህን ሀገራዊ ጥሪ በመቀበል ትግሉን አንድ እርምጃ ለማራመድ የሁሉም ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንዲረባረብ የሰሜን አሜሪካ ኢሕአፓ ክፍል ጥሪውን ያቀርባል። ሕዝባችን ከዚህ ከጎጠኛ ወያኔ ቡድን ለመላቀቅ እየከፈለ ያለውን መሰዋዕትነት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርና የታሪክም ተጠያቂዎች እንዳንሆን በአንድነት በመነሳት ትግሉን በተቻለን መጠን እናጠናክረው። **"ድር ቢያብር አንበሳን ያስር"** እንድሚባለው ሁላችን ተባብረን በአንድነት ከተነሳን ሀገራችን ኢትዮጵያን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከወያኔ ጎጠኛ ቡድን እናላቅቃታለን።

በመጨረሻም የሀገራችን ሉአላዊነት፣ የሕዝቧ የሥልጣን ምንጭነት በሕግ የሚረጋገጥበት፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝብና የሀገር አንድነት የሚጠበቅበት፣ የእምነትና የሃሳብ ነፃነት የሚከበርበት፣ በሕዝቡ ነፃና ርቱአዊ ምርጫ የሚካሄድበት ለማድረግ የማንኛውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሃላፊነትና ግዴታ እንዳለበት በማመን በሀገራችን ላይ አንጃቦ ያለውን አደጋ ለመቋቋም ሁላችንም በአንድነት በመነሳት የገንዘብ እርዳታ በማድረግ ትግሉን እንዲናጠናክር እነሆ የሰሜን አሜሪካ ኢሕአፓ ክፍል ጥሪውን ያቀርባል።

ኢትዮጵያ በታጋይ ልጆችዋ ነፃ ትወጣለች

---


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC. 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-Mail: Espic@aol.com
Website: WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France